ምኞት

እንዲሁም ሆኖ

ሰውየው በድህነት የሚማቅቅ ነው:: ምናምኒት የለውም:: ነገር ዓለሙ ባዶ ሆኖበታል:: አንድ ቀን ቃድያ እንደምንም ብሎ ያንን የፈራውን ልመና ሊያያዘው ጎዳና ይወጣል:: መቼም አያድርስ ነው ችግርን:: «አባቶቼ ስለ ወንድ ልጅ አምላክ» ይላቸዋል አንድ አዛውንት ከዘራ ቸውን እያስቀደሙ በአጠገቡ ሲያዘግሙ:: ኪሳቸውን ዳበስ፣ ዞር ብለው ገልመጥ ያደርጉና ስሙኒ ወርወር ያደርጉለታል:: ለምኖ ለማያውቅ ሰው ስሙኒ ትልቅ ናት:: ሲሮጥ ሲሮጥ ቤቱ መግባት:: ቤት እንበለው መቼስ ከወንፊት ያልተሻለ ጣራ ከበረት አጥር ያልተሻለ ግድግዳ አለው:: ካንድ ባዶ መደብ ምራቂ ጋር::

«አሁን በዚች ስሙኒ ምን ላድርግባት» ጭንቀት «አሁን በዚች ስሙኒ ምን ላድርግባት» ጭንቀት ላስታግሥ? ዱብ አለበት:: «ባኒ/ዳቦ/ ገዝቼ የሆዴን ሮሮ ላስታግሥ? የለም ላጠራቅማት:: ማን ያውቃል ነገ ሀብታም እሆን ይሆናል::» መቼስ ልብ አይሞት ይባል የለ:: «አዎ» ላምባ /ነዳጅ/ ልግዛባት አሁን ብላቱ ተገለጠልኝ::»

ሲከንፍ— ሲከንፍ— ሲከንፍ— የአምስት ሳንቲም ብልቃጥ ገዝቶ የ15 ሳንቲም ላምባ ሞልቶባት ወርቅ ዘርፎ እንደሚያመልጥ ሰላቶ በጉያው ደብቆ ቤቱ ከች::

«አሁን» አለ ሰውየው መደቡ ላይ ላምባ የያዘችውን ብልቃጥ አስቀምጦ:: መጀመሪያ ገበያ

«አሁን ይህችን ላምባ እየዞርኩ «ላምባ አወጣታለሁ:: ከዚያ ወዲያ በየጉሊቱ

የሚገዛ፣ ነጶ የማያልቅ በርቶ የማይጠፋ፣ ካማርካን የመጣ» እያልኩ አለፍሩለሁ:: መቼም ድምጤ የሰጠ ነው:: የገበያው ሰው ሁሉ አንገቱን መለስ ቀለስ፣ጉንበስ ቀና፣ ዘመር ዘመርመር፣ ገልመጥ ገልመጥመጥ እያለ «የቱ ነው? አይ ድምጥ እቴ» ሲለኝ እኔ ወንጶ ደግሞ ጅግን- ኩርት ቀብረር- ጉምለለለለል- እያልኩ ደረቴን የሠፌራ ችን አስኳላ ጥቁር ሰሌዳ አስመስዬ መሐል አራዳው ላይ ገጭ ያልኩኝ ጊዜ ያ ሲፈልገኝ የቆየው ገበያተኛ ሁሉ እንደንብ ሠራዊት አንዴ በላዬ ላይ ሲሰፍርብኝ «ሽዲያ ስንት ነው? የቱ ነው?እስቲ አምጣው» የጥያቄው ብዛት! እኔም ያባ ቢላ ልጅ ምኔ ሞኝ ነው፡ የንጉሥ አንበሳ መስየ «ዝግ በሉ ራቅ ራቅ በሉ፣ እንዲያውም ተሰለፉ፣ የለም እንዲያውም በጨረታ ነው የምሸጠው» እያልኩ ያን ሁሉ መንጋ ከቀኝ ከግራ ሳዋክበው እኔ ነኝ ያለ መኳንንት ዳቦ ቤት እንደተሳከ ኩታራ የቀን እኩሌታ መንገድ የሚያህል ሰልፍ ሠርቶ ቁጭ::

«መነሻው መቶ ሽልንግ ነው::» ብዬ እንደመብረቅ የሚንጉዳጉድ ድምጤን ሳስተጋባ ይች መናጢ ድኻ ሁላ «ታቅማችን በላይ ነው» እያለች ሰልፏን ለቃ ስትወጣ ከብር የተሠራ ያገሬ ዲታ ሆድ ለሆድ እየተጋፋ ሲጠጋኝ ጸጥታ ፣ ጸጥታ «መነሻው ሁለት መቶ ሺልንግ ሆኖአል::» ስላቸው የተራረፈው ድኻ ምንጥቅ ምንጥቅ እያለ ሲወጣ በሁለት እጅ የማይነሡት ብቻ ሲቀሩ፣ ቅልጥ ያለ ጨረታ አወጣና በአምስት መቶ ሺልንግ ሲያነሡልኝ::

እኔ የሰውየው ልጅ ከዚያ በኋላማ ማን

Scanned by CamScanner

ይናገረኛል:: በብልቃጥ መነገዱ ይቀርና በበርሜል ከብላምባራስ ደርበው ዴፖ እያመጣሁ፤ በሠረገላ አስጭንና ሁለት አሽከር ከግራ፣ ሁለት አሽከር ከቀኝ አስከትልና እኔ በሌላ ሠረገላ ከፊት እየቀደምኩ ኩራ ጀነን ለጠጥ ብዬ «በሀብቱ የሚተማመን፣ ድህነት ነክቶት የማያውቅ ወደኔ ወደ አባ መስጠት ይምጣ ካማሪካን፣ ካሮፖ፣ ከጃባን ተጣርቶ የመጣ ላምባ ማንም ሳይቀድማችሁ ግዙ! ያልኩን ጊዜ መንጋ ድኻ በሩቅ ሆና የሰውየውን ልጅ እዩትማ አሁን ይኼንንም ሞት ይነካዋል? እግዜር እጁን ታጥቦ የፈጠረው፣ እያለ ዕውቅ ደብተራ እንኳን የማያወጣውን መወድስ ሲያዘንብልኝ፣ ከቆዳው ላይ እግዜር ገንዘብ ያለበሰው ዲታ እንደ ፋሲካ ሙክት እየተ ጋፋ ይመጣና «ኖር ጌቶች፣ ኖር ጌታየ»እያለ እንደ ሰባሰገል ሲሰግድልኝ ለፈቀድኩት እጄን፣ ላልፈቀድኩት ጫማየን እያሳምኩ፤ ከኪሱ ቡላ ተቀይ ብር እየመዠለጠ ሲሰጠኝ በግራ እጄ እየተቀበልኩ እንደዋዛ ወደ ሠረገላየ ወርወር አደርግና ባስር ደቂቃ አጣርቼ ቤቴ ከች::

ተውኝ እባካችሁ:: በሚቀጥለውማ በራሴ መርከብ ከሳውዲ አረቢያ አስጭኚ አራት በአራት ሜትር በሆነ ባንዴራ ፎቶዬ ይሰቀልና በመርከቤ ላይ እየተውለበለበ የስ ማይ አዕዋፍ፣ ሳይቀሩ ምንም ስሜን ባያውቁ በግርማ ሞገሴ እያደነቁኝ ጉንበስ ቀና ብለው መርከቤን ሲሸኙዋት ማን ይጠጋኛል:: እኔ የሰውየው ልጅ::

አይ እግዚሀር እንዴ..ያ በድህነት እንደተጫወትክብኝ ዛሬ እኩል ሆንን! በሰማይ መንበርህ

እንጂ በምን ትበልጠኛለህ፡፡ እኔን የመሰለ ሰው ከማንም ድኻ ጋር ስንት ዘመን ጉለትከኝ? ወንድ ነኝ ታዲያ ደረስኩብህ! ባርያ ብትል ብበልጥህ እንጂ አሳንስም ገንዘብ? እንዲያውም ባለፈው ሰሰማ ያለም ባንክ መሪ ሲ ያስፈልጉኝ ነበር አሉ፡፡ ሰው መፍጠር ምን ያለፋኛል አንተ የፈጠርከውን አርፌ አልገዛም፡፡

አሁን መሐል ከተማ ቢላ ቤቴን እተክልና፡፡ ስንት ሚስት ላግባ? እኔን የመሰልኩ ሰው ባንድ ሚስት ተጠፍሬ ማ ምኑን ዲታ ሆንኩት፣ ሰው አራት ሚስት ታላገባ፣ ስድስት ዕንቁባት ታልያዘ፣ አምስት መኪና ካልገለበጠ፣ በቀን ሦስት ሺህ ብር ታልበተነ፣ ሆዱ እግሩን ለማየት ካልከለከለው፣ አንገቱ እንደ ስድስት ኪሎ ሐውልት ተተክሎ ታልቀረ፣ አንገትና ግንጭሉን መለየት ታላቃተ ምኑን ዲታ ሆነው! ድፍን ኢትዮጵያ ጉድ እስኪል ስድስት ሚስት አግብቼ እንደ ንብ ንግሥት ካልከበቡኝ እንደ ማንም ተራ መቆጠሬ አይደል?

ከዚያስ–

በከተማው የታወቁ ባለቡና ቤቶችን ሰብስባ እጠራ ለሁ፡፡ ከዚያ ወይዛዝርቱን ቅልጥ ባለ ግብዣ አንበሽብሻቸውና ኩስተር፣ ኩምተር፣ ኮራ ቆጠብ ያሉትን፤ ወገብና አንገታቸው በቦታ የሚጣሉባቸውን ስምንት ወይዛዝርት መርጬ በዕቁባትነት አስቀምጣለሁ፡፡ ምን ይኼ ብቻ ተሠራ የተባለ ቀርቶ ታሰበ የተባለ መጠጥ ከቤቴ አይጠፋም፡፡ መጠጣት ነው መስከር ነው፣ መጠ ንበዝ ነው፡፡ ውኃ ውኃ መሽተት ድሮ ቀረ፡፡ ወንድ ልጅ ካልሠከረ ሆዱ ዓሣ ይሠራልኩ! ከዚያ በኋላ ገንዳ ነው ብሉ ዓሣ ኮርፖሬሽን ቢረከበኝስ? ምኔ ሞኝ ነው፡፡

Scanned by CamScanner

መቼም ይኼ የኔቢጤ ሁሉ ግቢየን መክበቡ አይቀርም ቡትቷቸው እንዳይነካኝ ዙሪያየን በአሽከሬ ታጅቤ ሣንቲም እየወረወርኩ በመሐላቸው ሳልፍ የሙገሳው መዓት፣ከዚያ የበለጠ እግዜርነት ከየት ይመጣል?ደግሞ ያ መናጢ ወድቄ የምቀር መስየው ደበደበኝ አይደል? ብስርቅ–ምናለ ሁለት በግ ናት:: ደበደበኝ አገር የሚንቀጠቀጥለትን ሻለቃ አስጠርቼ ሁለት ዐመድ /ሃምሳ ሃምሳ ብር/ ቀጥለትን ሻለቃ አስጠርቼ ሁለት ዐመድ /ሃምሳ ሃምሳ ብር/ እሸጉጥለትና ከግራ ከቀኝ እያዳፉ ቡልስ ግቢያ ሲያገባው ያኔልኬን ያውቀዋል:: ምን እሱ ብቻ እነ ወንዳጥር፣ እንአቻሜለሽ፣ እነ ደባልቄ እነ ቢራራ «ደረቅ እግር» ብለው የሰደቡኝ ማን ደረቅ እንደሆነ አሳያቸዋለሁ:: ዛሬ ተሠርተው የመሰሉ ሁለት ጠብደሎች ቀጥሬ ማረኝ ጭቃቸው ያልደረቀ የመሰሉ ሁለት ጠብደሎች ቀጥሬ ማረኝ ይቅር በለኝ አርባ አንድ ጊዜ እስኪሉ ድረስ በተረት የሚያውቁትን የጥርሳቸውን ቁጥር ያላስጠናኋቸው እንደሆን እኔ አይደለሁም::

በመንገድ ሳልፍ ያየኝ ካልተደፋ:: አጭሩ ዛፍ ላይ ወጥቶ፣ ረዥሙ ተንጠራርቶ፣ የታዘለው አንቀልባ ፈትቶ፣ ታሞ የተኛው ዱላ ተደግፎ፣ የሚድኸው ታቅፎ እንደታቦት ካልተሳለመኝ እኔ አይደለሁም::እንዲህ ሕዝበ አዳምን ሳስግደው ውየ ወደ ቤቴ የገባሁ ጊዜ ስድስት ሚስቶቼ አንዷ ምግቤን፣ አንዷ መጠጤን፣እያሉ ሲዋከቡ በአባ ወራ ወግ አልጋየ ላይ ጋደም ብዬ...

መደቡ አልጋው መስሎት ጋደም እላለሁ ሲል በእግሩ ብልቃጧን ቢመታት ያች የአስራ አምስት ሳንቲም ጣራና ግድግዳው ከትከት ብሎ የሚስቅ «አንዱንም ሳትይዝ ከሁሉም ጋር ተጣልተህ የተንዝከበት የምኞት ፈረስ እንዲህ ከሁሉም ጋር ተጣልተህ የተንዝከበት የምኞት ፈረስ እንዲህ ጉድ ይሥራህ» የሚሉት መሰለው:: አይ የምኞት ፈረስ............?